በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ ማዕ/ጎ/ሀ/ስ ለደብረ ታይል ወደብረ ጥበብ በአታ ለማርያም የተሰጠ

የነገረ ቅዱሳንና የነገረ አበው ኮርስ



አዘጋጅ፡- በትረ ማርያም አበባው

(የመጻሕፍተ ብሉያት፣ የመጻሕፍተ ሊቃውንትና የመጻሕፍተ መነኰሳት ትርጓሜ መምህር)

መስከረም ፳፮፣ ፳፻፲ዓ.ም

ነገረ ቅዱሳን

ይህ ትምህርት ስለቅዱሳን የምንማማርበት ክፍል ነው፡፡ ነገረ ቅዱሳን የመንፈል ገጢራዊ (ሕይወታዊ) ትርጓሜ ነው፡፡

ቅድስና

ቀዳሰ=አመሰገነ፣ለየ፣መረጠ ከሚለው የግእዝ ቃል ቅድስና የሚል ጥሬ ምስጋድ ይወጣል፡፡ መመረጥ፣መለየት፣መመስገን...ማለት ነው፡፡ ቅድስና የባሕርይ ቅድስናና የጸጋ ቅድስና ተብሎ ለሁለት ይከፈላል

የባሕርይ ቅድስና

የባሕርይ ቅድስና ያለው እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡ ይኸውም እግዚአብሔር ቅዱስ ነው ስንል ቅድስናውን ከሌላ ያላገኘው፣ ለዘመን ብዛት የማይለወጥ ነው ማለታችን ነው፡፡

የጸጋ ቅድስና

ጸገመ=ሰጠ ከሚለው የግእዝ ቃል ጸጋ የሚል ጥሬ ዘር ይወጣል፡፡ ይኸውም ስጦታ ማለት ነው፡፡ ለፍጡራን ያላቸው ቅድስና የጸጋ ቅድስና ነው፡፡ ይኸውም የእግዚአብሔርን ሕግ ለመጠበቃቸው፣ ለእግዚአብሔር ተለይተው ለመስጠታቸው ምክንያት የሚሰጥ ነው፡፡ እግዚአብሔር ቸር ለመሆኑ ለእርሱ የባሕርይው የሆኑትን ለፍጡራን ደግሞ ለጸጋ ይሰጣቸዋል፡፡

- ኢየሱስ ከክብ እንደተባለ ቅዱሳንም ከክብ ተብለዋል
  (ዘኍ.24÷17 ፤ ራእ.22÷16 ፤ ዳን.12÷3)
- ኢየሱስ መልካም እረኛ እንደሆነ ጻድቃንም መልካም እረኞች ይባላሉ
  (ዮሐ.10÷11 ፤ ዮሐ.21÷15-17)
- ክርስቶስ ብርሃን እንደተባለ ጻድቃንም ብርሃን ይባላሉ
  (ዮሐ.9÷5 ፤ ዮሐ.12÷46 ፣ ማቴ.5÷16)

ለእግዚአብሔር ለኢየሱስ ክርስቶስ የተነገረው የባሕርይ ሲሆን ለሰዎች ለፍጡራን የተነገረው ደግሞ የጸጋ ነው፡፡

የቅዱሳን ተጋድሎ

ተጋድሎ ማለት ቅዱሳን ስለ ሃይማኖት ሲያስተምሩ ለክፉዎች ነገሥታትና ለሐሰተኛ ሰዎች መክሪን መቀበል ማለት ነው። አጋንንትን ፣ ነፍስን የሚያውኩ አኩያት ፍትመታትን፣ ኃጣውእን ለመቋቋም መስኖ ለድናት መጋደልም ተጋድሎ ይገኅል። ሌተ ክርስቲያን ለዓላውያን ነገሥታት ፣ ለአረማውያን መኳንንት ፣ ለመናፍቃን ሤራ ስትፈተንና ስትገፋ ብትኖርም እስከዚህ ትውልድ ያደረሳት የእግዚአብሔር ቸርነትና የቅዱሳን ተጋድሎ ነው።

ቅዱሳን መክሪን የሚቀበሉት ከማን ነው?

- ከፈቃደ ሥጋ (ገላ. 5÷16-17)
- ከዓላውያን ነገሥታት (ማቴ. 10÷17-18)
- ከመናፍቃን (የሐዋ. ሥራ 20÷29-30)
- ከጠንቋዮች (የሐዋ. ሥራ 13÷10)
- ከአሕዛብ (2ኛ ቆሮ. 11÷26)
- ከአጋንንት (ኤፌ. 6÷10-18)

ቅዱሳን ለዚህ ሁሉ ሊፈተኑም እስከ ምት ድረስ ለእግዚአብሔር ለመታመን ኖረዋል (ራእ. 2÷10)።

ነገረ ቅዱሳንን የመማር ጥቅም

ቅዱስ ጳውሎስ ለዕብራውያን መልእክቱ ከአቤል ጀምሮ ያሉትን ቅዱሳን ስማቸውን እየጠራ ፣ ታሪካቸውን እየተረከ የሰብክቱ አካል አድርጓቸዋል። መንፈሳዊው ሉቃስም መንፈሉን ሲጽፍ የዘካርያስንና የኤልሳቤጥን ቅድስና ለመጥቀስ ነው። ለመሆኑም ነገረ ቅዱሳንን መማር ጥቅሙ፡-

- ለመልካም ሥራዎቻቸው አርአያ ለማድረግ (ዕብ. 13÷7)
- ከቃል ኪዳናቸው ለመጠቀም
- ለዘመናቸው ከገጠማቸው ፈተና የመጡበት መንገድ ለዘመናችን ለሚያጋጥመን ፈተና መውጫ አርአያ እንዲሆነን

የቅድስና ዐብይት መስፈርዎች

ገድላቸውን ለፈጸሙ ቅዱሳን ክፅረፍታቸው/ክምታቸው በኋላ ሥራቸው ተመዝኖ መዓርገ ቅድስና ተረጋግጦ ይሰጣል። ይህም ለይፋዊ ቀኖና (Official Canonicity) ወይም ለትውፊታዊ ቀኖና (Traditional Canonicity) ሊሆን ይችላል። ዋና መመዘኛዎች የሚከተሉት ናቸው።

- ሃይማኖትን በመጠበቅና በማስጠበቅ ያለረክቱት አስተዋጽኦ
- ለገዳማዊ ሕይወት ለመጽናት፣ ተአምራትን ለማድረግ ያለረክቱት አስተዋጽኦ
- ለእውነት ሰማዕት መሆን
- የተለያዩ መንፈሳዊ አገልግሎትን ለመፈጸም ያደረጉት አስተዋጽኦ
- እስከ ሕይወታቸው ፍጻሜ ድረስ ለጾም፣ ለጸሎት ተወስነው ለአምልኮተ እግዚአብሔር መጽናታቸው
- የእግዚአብሔርን ቃል ንገብ፣ ትርጓሜና ምሥጢር ሳያፋልሱ ለማስተማር መጽናታቸው
- ለሕይወታቸው ነውር ለሃይማኖታቸው ነቀፌታ ያልተገኘባቸው መሆናቸው

ለቅዱሳን ምን እናደርጋለን?

አንድ ቅዱስ ቅዱስ ተብሎ ከተሰየመ በኋላ የሚከተሉት ነገሮች ይደረጉለታል።

- ሕይወቱ ለገድል መጽሐፍ እንዲጻፍ ይደረጋል (ማቴ.26÷13)
- መልክዕ ይደረስለታል
- የመታሰቢያ ቀን ይወሰንለታል፣ የመታሰቢያ ሠዓል ይሣልለታል
- ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን ለስሙ ይታነጽለታል (ኢሳ.56÷4)
- ለስሙ ጽላት ይቀረጽለታል
- ለስሙ እንማፀንበታለን
- የተለያዩ መንፈሳዊ ስያሜዎችን እንሰይም ባቸዋለን

የጻድቃን መታሰቢያ ለዘለዓለም ይኖራል (መዝ.111÷6)፣ የጻድቅ መታሰቢያ ለበረከት ነው (ምሳ.10÷7)። ቅዱሳንን አክብሮ መቀበል መንፈሳዊ ዋጋ ያሰጣል (ማቴ.10÷40-42)። ለገድላት ለድርሳናት መጻፍ መሠረቱ መጽሐፍ ቅዱስ ነው።

ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ የቅዱሳን መገኛ ክብሩ
የቅዱሳን ሰዎችን ክብረቸውን፣ ተሰጥኦቸውን፣
የተራድኦ ዜናቸውን እንደሁም ከእግዚአብሔር
ዘንድ የተሰጣቸውን ቃለ ኪዳን ይገልጻልና።

ለመጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር አምላክ
ተብሏል። የእግዚአብሔር ኩምላክነት የባሕርይ
ኩምላክነት ነው። ቅዱሳንም ለጸጋ ኩማልክት ይባላሉ
መዝ.49÷1 ላይ የአማልክት አምላክ እግዚአብሔር
ተናገረ ሲል ኩማልክት የተባሉ ቅዱሳን ናቸው።
እግዚአብሔር ሊቀ ነቢያት ሙሴንም የፈርዖን
ኩምላክ አድርጌ ሃለሁ ብሎታል (ዘፀ.7÷1)።

ቅዱሳን

ከፍጡራን ቅዱሳን እየተባሉ የሚጠሩ የሚከተሉት
ናቸው።

- ቅዱሳት መካናት (ቦታዎች)
- ቅዱሳት ለባላት (ጊዜያት)
- ቅዱሳት ንዋያት
- ቅዱሳት ሠዕላት፣ መጻሕፍት...
- ቅዱሳን መገኛት
- ቅዱሳን ሰዎች ናቸው።

ቦታዎች ቅዱስ ለመባላቸው ኢያ.5÷13-15
የቆምክበት ስፍራ የተቀደሰች ናትና ጫማህን
ኩውልቅ ተብሎ ተገልጿል። እንደሁም ኢየሱስ
ክርስቶስ ግርማ መለኮቱን የገለጸበት የደብረ ታቦር
ተራራ ቅዱሱ ተራራ ተብሏል (2ኛ ጴጥ.1÷16-18)።
ይህን መሠረት ለማድረግ ቅዱሳን ተጋድሏቸውን
የፈጸሙባቸውን ቦታዎች ቅዱሳት መካናት እያልን
እንሰይማቸዋለን። በተጨማሪም እግዚአብሔርን እንድ
ናክብርባቸው የተመረጡ የለባላት ጊዜያት ቅዱሳት
ይባላሉ (ዘፀ.31÷15)። ነገረ እግዚአብሔርን የሚናገሩ
መጻሕፍትም ቅዱሳት ይባላሉ (2ኛ ጢሞ.3÷15-17)።

ቅዱሳት ንዋያት

ለቤተ እግዚአብሔር አገልግሎት ተለይተው የሚያገለግሉ ንዋያት ንዋየ ቅድሳት ይባላሉ። ወደ ቤተ እግዚአብሔር የገባን ንዋይ ቅዱስ ለግል ዓላማ መጠቀም አይቻልም። ብልግሶር ለቤተ መቅደስ ንዋያት ፈትፈዱ ስለለብባቸው፣ ስለጠግባቸው መቅሠፍት ደርሶበታል (ፍት. ካገ. 1 ፣ ዳን. 5÷2-9)።
(ዘዳ. 30÷22-29)

ቅዱሳት ሥዕላት

ለቅዱሳን ስም የተሳሉ፣ ትምህርተ እግዚአብሔር የሚገልጹ ሥዕላት ቅዱሳት ሥዕላት ይባላሉ። ልዑል እግዚአብሔር ቀድሞ ለሙሴ ለደብተራ ኦሪት ለኋላም ለጠቢሉ ሰሎምን ለቤተ መቅደስ ሥዕለ ኪሩብን እንዲሥሉ አዝዟቸው ነበር። እነርሱም ለሣሉት ሥዕል ፈት ሆነው ወደ እግዚአብሔር ጸልየው ጸሎታቸው ተሰምቷል (ዘፀ. 25÷21-22 ዘኍ. 7÷8-9)። ይህም ለቅዱሳት ሥዕላት ፈት ቆም መጸለይ እንደሚገባ ያስተምረናል (ዘፀ. 21÷1፣ 1ኛ ነገ. 6÷23 ፣ 2ኛ ዜና መዋ. 7÷11-12)።

ለሐዲስ ኪዳን የክርስቶስን ስቅለት ለጢባር ዮስ ቄሣር ለማሳየት ሐዋርያው ዮሐንስ ስሎታል። ለዕለተ ሰቅለቱ ደሙን ይጠርግለት ዘንድ ኀሥ ፲ሮኒካ ለሰጠችው 2ዜ የፊቱ ሥዕል ለኀሥ ተቀርፃል ኅንታዊ ክርስቲያኖች ለግለ ምድር ውስጥ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮችን የሚገልጹ ሥዕሎችን ይሥሉ ነበር። ለሥዕል ወንጌልን ማስተማር ይቻላል። ለሥዕል ፈት ኅማ ስናበራ ለሥዕለ እግዚአብሔር ፈት ሲሆን እግዚአብሔር ለገሕርይው ብርሃን መሆኑን ለመግለጽ ነው። ቅዱሳን ቢሆኑ ለጸጋ ብርሃን መሆናቸውን ለመግለጽ ነው።

(ማቴ.5÷14)፡፡ ለብሉይ ኪዳን መንበሩን የሚሸክሙ ኪሩ ቤል ሥዕል በቤተመቅዳስ እንዳነበረ ሁሉ ለሐዲስ ኪዳን ደግሞ አምላክን ዘጠኝ ወር ካአምስት ቀን ለማኅፀኑ የተሸክመች የድንግል ማርያም ሥዕል በመቅዳስ ይቀመጣል፡፡

ቅዱሳን መጎእክት

የእግዚአብሔርን ጸጋ ወዳ ሰው የሰውን ጸሎትና መሠዋዕት ወዳ እግዚአብሔር የሚያዳርሱ፣ ዕረፍታቸው ምስጋናቸው፣ ምስጋናቸው ዕረፍታቸው የሆኑ ረቂቃን ፍጥረታት ናቸው፡፡ (ዳን.9÷22፣ የሐዋ.ሥራ 10÷4)፡፡ ቅዱሳን መጎእክት፡-

- ያድኑናል (መዝ.33÷7)
- ይረዱናል (ዳን.10÷21)
- ያማልዱናል (ዘካ.1÷12-17)
- ጸሎታችንን ያሳርጉልናል (የሐዋ.ሥራ 10÷1-4)
- ይዋጉልናል (ራእ.12÷7)
- ይጠብቁናል (መዝ.9÷10-12)
- ለንስሓችን ዳስ ይገቸዋል (ሉቃ 15÷8-10)
- ይመግቡናል (1ኛ ነገ.19÷1-8)

ቅዱሳን ሐዋርያት

መንፈልን ለፍጥረት ሁሉ ይሰብኩ ዘንድ ለፈታችን ለመድኃኒታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ የተመረጡ 12 ሰዎች ናቸው (ማቴ.28÷20)፡፡ ሐዋርያት ብዙ መከራዎችን ለመቀበል፣ አይሁድ እያሴዙባቸው፣ እስከ ሞት ለመታመን መንፈልን አስተምረዋል፡፡ ለሐዋርያት እግር ተተክተው መንፈልን ያስተማሩ ደግሞ ሐዋርያውያን አበው ይባላሉ፡፡

ቅዱሳን ሰማዕታት

ለዓላውያን ነገሥታት ፊት ቀርበው ጎያፍሩና ጎደፈሩ አለፈጣሪ የመሰከሩ ሰማዕታት ይባላሉ፡ አለሃይማኖታቸው አለእግዚአብሔር ክብር ብለው ደማቸውን ያፈሰሱ፣ አጥንታቸውን የከሰከሱ፣ አይወታቸውን የሰጡ ናቸው

ሰማዕት ማለት ምስክሮች ማለት ነው። ለእግዚአብሔር ስለክርስቶስ የመሰከሩ ናቸው። ስለሃይማኖታቸው ሊያስተምሩ ለሐሰተኞች ተሰቃይተዋል፣ ለአካሉ ደያን እድ ምተዋል። ነፍሳቸው የሚወጡ እስኪያት ፍትወታትን፣ ኃጣውእን ለመቋቋም ተጋድለዋል። በሰይፍ ተመትረዋል፣ ለመጋዝ ተተርትረዋል፣ ለእሳት ተቃጥለዋል፣ ለአናብስት ተጥለዋል፣ ለአጠቃላይ ለብዙ አቃያት ተፈትነዋል። ሰማዕታት "ሥጋንም የሚገድሉትን ነፍሳን ግን መግደል የማይቻላቸውን አትፍሩ" የሚለውን የጌታ ቃል መሠረት አድርገው ስለእግዚአብሔር ለእውነት የኖሩ ናቸው (ማቴ.10÷28)። ሰማዕትነት ለሁለት ይከፈላል። እነዚህም አረንጓዴ ሰማዕትነት (Green Martyrdom) እና ቀይ ሰማዕትነት (Red Martyrdom) ናቸው። **አረንጓዴ ሰማዕትነት** የሚባለው አካሉታዊ ፈተና (እኩያት ፍትወታትና ኃጣውእ) ጋር የሚደረግ ትግል ነው። ክፋትን፣ ምቀኝነትንና ሌሎችንም ኃጣውእ ለማስወገድ ለጽኑ ጾም፣ ለጸሎት፣ ለስግደት፣ ለትሕርምት፣ ለንስሓ ሕይወት ለመቀጋት የሚደረግ ተጋድሎ ነው። ለዚህም አተድገ ሠጋ ርቀው፣ ለትጋሄ ሌሊት፣ ለዐቂበ ሕዋሳትና ለትሕትና ጸንተው ይኖራሉ። **ቀይ ሰማዕትነት** የሚባለው ስለ እግዚአብሔር፣ ስለቤተክርስቲያን፣ ስለመንግሥተ ሰማያት ያእካለና የኅሊና ስቃያትን (physical and mental Sufferings) መቀበል የሕይወት መሠዋዕትነትን መክፈል ነው። ዓመተ ሰማዕታት የሚባለው አዲዮቅልጥያኖስ ዘመነ መንግሥት (284 ዓ.ም) ጀምሮ የታየነሣ አቆጣጠር ነው። ከቅዱሳን ሰማዕታት መካከል ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው።

- ቅዱስ ጊዮርጊስ
- ቅዱስ ፊቅጦር
- ቅዱስ ገላውዴዎስ
- ቅዱስ ቴዎድሮስ
- ቅዱስ አባ ሚና
- ቅዱስ አቦሊ
- ቅዱስ ሩፉለጸለ
- ቅዱስ መርዓና
- ቅዱስ ቂርቆስ
- ቅዱስ አባዲር
- ቅዱስ መርቆሬዎስ
- ሺህ ሐራ ሰማዕታት
- ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘአርመንያ ሰማዕት ዘእንስጣስ ክፅመተ ይቆጠ

እረንጓዴ ሰማዕትነት ሰማዕትነት ዘእንበለ ክህወት ደም እየተባለ ይጠራል፡፡

ቅዱሳን አበው

ለሕገ ልቡና ፈጣሪያቸውን እግዚአብሔርን ያገለገሉ አባቶች ቅዱሳን አበው ይባላሉ፡፡ ምሳሌ አብርሃም፣ ይስሐቅ፣ ያዕቆብ፡፡

ቅዱሳን ነቢያት

ሀብተ ትንቢት ከእግዚአብሔር ተሰጥቷቸው ባለፈው ዘመን የተደረገውን፣ አሁን ያለውንና መጻፊት የሚመጣውን ለእርግጠኝነት የተናገሩና የሚናገሩ ናቸው፡፡ ቅዱሳን ነቢያት ትንቢትን ከመናገር በተመማሪ በዘመናቸው የነበረውን ንጉሥና ሕዝቡን ያስተምሩ ነበር (2ኛ ጴጥ.1÷21 ፣ ማቴ.10÷41)፡፡

ቅዱሳን መነኰሳት

ከሕገ እንስሳ ሕገ መላእክት ይበልጣል ብለው ለድንግልና ተመስነው መይም ዓለምን ንቀው፣ ስለመንግሥተ ሰማያት ብለው ራሳቸውን ጃንደረቦች ያደረጉ ናቸው (1ኛ ቆሮ.7÷32-34)፡፡ መለ ዘመናቸውን መይም ከመነኰሱበት ጀምሮ ከጣዕመ ዓለምና ከተድላ ዓለም ተለይተው በምናኔ ጸንተው የኖሩ ናቸው (ዕብ.11÷37-38)፡፡ መነኰስ ማለት ከዓለም የራቀ መናኝ ማለት ነው፡፡ የመነኰሳት ቆባቸው የእክሊለ ሠክ፣ ቀሚሱ የክለሜዳ፣ ቅናቱ የሐብል ምሳሌ ነው፡፡ ምንኵስና ሠስት ዓይነት ሥርዓት አለው

→ ድውይ ዘለአኰቴት፡- ደዌውን በምስጋና የሚቀበል
→ ገሕቲዊ ዘለጓድዐት፡- ለጸጥታ፣ ለዝምታ፣ ለሜምትነት ብቻን መኖር
→ ረድዕ ዘለጥብዐት፡- ቆራጠ አገልጋይ፣ የራሱን ፈቃድ ትቶ የሌሎችን መልካም ፈቃድ የሚፈጽም፡፡

ከቅዱሳን መነኰሳት ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

- አባ ጳውሊ
- አባ እንጦንስ
- አባ ጳኵሚስ
- አባ መቃርዮስ ዘየዐቢ
- አባ መቃርዮስ ዘቆቅሕ
- አባ ዘሲማስ
- አባ አርሳንዮስ
- አባ ዮሐንስ ሐፀር
- ቅድስት ሂላርያ
- ቅድስት እንባ መሪና
- ቅድስት ማርያም ግብፃዊት
- አባ አምን



ለሀገራችን ምንኵስናን የመሠረቱትና ያስፋፉት ተስዓቱ ቅዱሳን ናቸው:: ከእነርሱ ለመቀጠል ለሀገራችን ለምንኵስና ከሚታወቁ ቅዱሳን መካከል ጥቂቶቹ:-

- አቡነ ተክለ ሃይማኖት
- አቡነ ኤዎስጣቴዎስ
- አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ
- አቡነ ሳሙኤል ዘዋልድባ
- አቡነ ዜና ማርቆስ
- አቡነ ሀብተ ማርያም
- አቡነ ሊባኖስ
- አቡነ ሐራ ድንግል
- አቡነ ተክለ አልፋ
- አገ ኢየሱስ ሞዐ

እነዚህ አባቶች ከምንኵስና ለተመማሪ መንጎልን ለማስተማር የደከሙ ናቸው:: አቡነ ተክለ ሃይማኖት ሐዲስ ሐዋርያ ኢየተባሉም ይጠራሉ::

ቅዱሳት አንስት

ባፍኖተ ክርስቶስ ተመርተው፣ ቅድስናን ገንዘብ አድርገው ስለ ክርስቶስ ሰማዕት የሆኑ፣ ይህንን ዓለም ንቀው የመነኰሱና ሌላም መንፈሳዊ ሥራን የሠሩ ሴቶች ቅዱሳት አንስት ይባላሉ:: ፈታውራሪያቸው እመሌታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ናት:: ከቅዱሳት አንስት ጥቂቶቹ:-

- 36ቱ ቅዱሳት አንስት
- ቅድስት ማክሪና
- ቅድስት ክርስቶስ ሠምራ
- ቅድስት መለተ ጴጥሮስ
- ቅድስት ማርያም ግብፃዊት
- ቅድስት ኢየሉጣ
- ቅድስት አርሴማ
- ቅድስት ሶፍያ
- ቅድስት ፍቅርተ ክርስቶ

ቅዱሳን ጳጳሳት

ምእመናንን፣ ካህናትን ይጠብቁ ዘንድ ቤተክርስቲያንን ያስተ
ዳድሩ ዘንድ የተሾሙ አገዶች ጳጳሳት ይባላሉ (የሐዋ.ሥራ.20÷28)
ቅዱሳን ጳጳሳት መናፍቃን ሲነሡ ተሰብስበው ትክክለኛዋን ሃይማ
ኖት ጠብቀው መናፍቃንን እያወገዙ የኖሩ ናቸው። በሀገራችን
በኢትዮጵያ ሃይማኖትን በማስተማር፣ሥርዓትን በማጽናት
የሚታወቀው የመጀመሪያው ጳጳስ አቡነ ሰላማ ክሣቴ ብርሃን
ነው። ለሃይማኖታቸውና ለሀገራቸው ክብር ሰማዕት የሆኑት
ደግሞ አቡነ ጴጥሮስ ናቸው።

ቅዱሳን ነገሥታት

በሥልጣናቸው፣ በሠራዊታቸው፣ በሀብታቸው ሳይመኩ
ሃይማኖትን ይዘው፣ ምግባር ሠርተው የተገኙ ነገሥታት ናቸው።
ትምክህታቸውን እንዳ ዳዊት በእግዚአብሔር ላይ በማድረግ
ሕይወታቸውን ለእግዚአብሔር በማስረከብ የጸኑ ናቸው።
የሚመሩትን ሕዝብ ፍርድ ሳያጋድሉ፣ ድኻ ሳይበድሉ፣ ጉቦ
ሳይቀበሉ፣ ለሰው ፊት ሳያዳሉ አስተዳድረዋል። ለምሳሌ
በሀገራችን ከተነሡት ቅዱሳን ነገሥታት የሚከተሉት ይጠቀሳሉ።

- አፄ ካሌብ
- አብርሀ መአጽብሐ (ኢዛናና ሳይዛና)
- አፄ ገብረ መስቀል
- ቅዱስ ይምርሐነ ክርስቶስ
- ቅዱስ ሐርቤ (ገብረ ማርያም)
- ቅዱስ ላሊበላ
- ቅዱስ ነአኵቶ ለአብ

ቅዱሳን ሊቀውንት

ቅዱሳት መጻሕፍትን በመተርጐም ምእመናንን ለሃይማኖት ያጸኑ
ናቸው። ከሓድያን የተሳሳተ ትምህርት ይዘው ሲነሡም ኃይለ
ቃል ጠቅሰው ተከራክረው የረቱ ናቸው። ሃይማኖት እንዳይጠፋ፣
ትምህርቱም እንዳይፋለስ ሌት ከቀን በማስተማር በርካታ ደቀ
መዛሙርትን ያፈሩ፣ አያሌ መጻሕፍትንም የጻፉ ናቸው።

ለሀገራችን ክርስትና መሰረት የሆኑትን መካከል የሚከተሉት ይጠቀሳሉ

- ቅዱስ ያሬድ
- ቅዱስ አባ ጰዮርዮስ ዘጋስጫ

ነገረ አበው
(Patrology)

ነገረ አበው የቤተክርስቲያን አባቶች ሕይወታቸው እና ትምህርታቸው የሚጠናበት የነገረ መለኮት ትምህርት ክፍል ነው። ተጽንዖቷ ቤተክርስቲያን ታሪክ የሚታመቁ አባቶችን ታሪክ መመቅ ስለጽንዖቷ ቤተክርስቲያን አምሰክት፣ መጓለ ራዊ ሕይወትና አጠቃላይ የመንፈሳዊ ሕይወት ታሪክ ለቀላሉ ለመረዳት ያስችላል። የቤተክርስቲያን አባቶች ቤተክርስቲያን አንድነት ጸንቶ እንዲኖር ለሚጠብቁት መንፈስ ቅዱስ ለሚታደ ገንዘብ ተገገሪቶች ጠባቂዎች ናቸው።

የትምህርተ አበው አስፈላጊነት

- ቅዱሳት መጻሕፍትን ተጉዕክሆ ለመረዳት
- ቤተክርስቲያንን ለማስረዳት
- የቤተ ክርስቲያንን ታሪክ ለመረዳት
- የክርስቲያናዊ ኑሮን ለመረዳት

እርዳታክሳዊውን አስተምህሮ ለቃለ ብቻ ሳይሆን ተግባር ያስተማሩትን የቤተ ክርስቲያን አባቶች እንተቸዋለን። ተነገረ አበው ትምህርት የአገልጎሎት ዕውቅና ለመስጠት አሬት መስፈርቶች የሚከተሉት ናቸው።

- ድርሳናቸውን መጻፍ
- እርዳታክሳዊ አስተምህሮ
- የሕይወት ቅድስና
- ቀደምትነት (ጥንታዊነት)

የቤተ ክርስቲያን አባቶች ተነስተናበት ዘመን ቅድመ ኀቅያ እና ድኅረ ኀቅያ ተብለው ይከፈላሉ። ተነሳናበት ቦታና ተጻፉበት ቋንቋ የሚከፈሉም አሉ። የማንኖሙም ሰው ትምህርት መመዘኛ ቅዱሳት መጻሕፍትና ቅዱስ ትውፊት ናቸው። ስለዚህ ይኸንኑ አባት ትመቀሳነት ከሠለቱ ጋር እስከተስማማ ድረስ ትክክል

ቅዱሳን አገራቸው ለኦርቶዶክሳዊው አስተምህሮ አንድ ቢሆኑም ለኖሩባቸው ዘመናት፣ቦታዎች፣ ባህሎችና ለገዘው የጸሊሎታቸው የጊዜ ልዩነት ያመላከታቸውን እውነትና እንረሱም አጸሪ አንጻር አንዳንድ ጉዳዮችን ለሚገልጹበት መንገድ የተለያዩ ሆነው እናገኛቸዋለን ይህም የአገላለጽ (Way of expression) ነው እንጂ የአስተምህሮ ለየኑት አይደለም።

የትምህርተ አበው ጥናት መርሆዎች

- አንድን አባት አጥንተው ዘመን ለይቶ መመደብ አይገባም። ስለሆነም ለዘመኑ የነበረውን ሃይማኖታዊ ሁኔታ መገንዘብ ያስፈልጋል።
- ለአንድ አባት ጽሑፍ ብቻ መወሰንና ለዚያ ተመሥርቶ ወደ ድምዳሜ መድረስ አይገባም።
- ነገረ ሃይማኖታዊ ቃላትንና መግለጫዎችን እንደ ዘመኑ ግብራቸው መመደብ
- አንድ አባት የተጠቀሰውን ቃል ለዘመኑ አነበሩ አጠራሩ አገው ጋር ማስተያየት (ማነጻጸር) ያስፈልጋል።

አበው

አበው ተብለው አጠቃላይ የሚጠሩ አባቶች ጥቂቶች የሚከተሉት ናቸው። ቅዱስ አትናቴዎስ ቅዱስ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ፣ ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ፣ ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ፣ ቅዱስ ያሕንስ አፈወርቅ፣ ቅዱስ ቄርሎስ፣ ቅዱስ ባስልዮስ፣ ቅዱስ ኤፍሬም፣ ቅዱስ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ፣ ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ፣ ቅዱስ ያሕንስ አፈወርቅ፣ ቅዱስ ቄርሎስ፣ ቅዱስ ባስልዮስ፣ ቅዱስ ኤጲፋንዮስ፣ ቅዱስ ሄሬኔዎስ... መዛግብት ናቸው።

የቅዱሳን አማላጅነት

አማላጅ ማለት ሰለሌላው የሚጸልይ የሚለምን ማለት ነው። (ዘፀ. 32÷31-32)። ቅዱሳን ለእግዚአብሔር ፊት ምግባን ያገኙ ባለሟሎች ናቸው። ምክንያቱም አግዚአብሔር የፈቀዱላቸው የፍቅሩ መገለጫ ነው። (ያዕ. 5÷16-18፣ ራእ. 8÷3-4፣ ዮሐ. 15÷29፣ 2ኛ ቆሮ. 9÷13-15)።

መዓርጋተ ቅዱሳን

መዓርጋተ ቅዱሳን ለሦስት ዐበይት ክፍሎችና ለዐሥር ንዑሳን ክፍሎች ይከፈላል። ለዐቢይ ንጽሕ ሠጋ፣ ንጽሐ ነፍስ፣ ንጽሐ ልቡና ተብሎ ይከፈላል። ለንዑስ ደግሞ ጽማዌ፣ ፀባዌ፣ ጣዕመ ዝማሬ፣ አንብዕ፣ ኵነኔ፣ ሐሴት፣ ፍቅር፣ ንጹሬ መላእክት፣ ተሰጥዎ ብርሃንና ነጋድያ አሳት ናቸው። የመጀመሪያዎቹ ሦስቱ የንጽሐ ሠጋ፣ ቀኝለው ያሉት አራቱ የንጽሐ ነፍስ፣ የመጨረሻዎቹ ሦስቱ የንጽሐ ልቡና መዓርጋት ናቸው።

፩. ጽማዌ፡- ለመናገር ካሚመጣ ኃጢአት መጠበቅ ነው
፪. ልባዌ፡- ቃለ እግዚአብሔር ልብ ማድረግ/ማስተዋል ነው
፫. ግዕመ ዝማሬ፡- ጎይሰለቹና ሳይቸኩሉ ምሥጢርና ትርጓሜውን እያስተዋሉ ለንቁ ኅሊና ማመስገን ነው
፬. እንብዕ፡- ሰውነት በኃዘን ሳይካፋ የሚፈስ እንባ ነው፡፡
፭. ኵነኔ፡- ፈቃዱ ሥጋን ለፈቃዱ ነፍስ ማስገዛት ነው፡፡
፮. ሑሰት፡- ካሉበት ቦታ ሆኖ ጠፈር ዱፈር/ግዘፍ ያለው ነገር/ ሁሉ ሳይካለክለው ካሰቡበት ዱርሶ የፈለጉትን ማወቅ ነው፡፡
፯. ፍቅር፡- ፍጥረታትን ሁሉ መውደድ ነው፡፡
፰. ንዓሬ መጎእክት፡- መጎእክትን ከነክብረቸው ማየት፣ ከእነርሱ ጋር ማመስገን ነው፡፡
፱. ተሰጥሞ ብርሃን፡- ለሚያስደንቅ ብርሃን ውስጥ መዋኘት
፲. ከዊነ እሳት (ነጽሮተ ሥሉስ ቅዱስ)፡- ሥጎሴን ለዘፈቀዱ ማየት ነው፡፡

የቅዱሳን ቃለ ኪዳን

ሁሉ እግዚአብሔር ከመሪጥኳቸው ጋር ቃለ ኪዳን እንደሚያድር ግ ነግሮናል (መዝ.88÷3)፡፡ እግዚአብሔር ለቅዱሳን ቃለ ኪዳን ይጠብቀናል (ዘፍ.9÷1)፡፡ የቅዱሳን ሁለንተናቸው የከበረ ነው፡፡ ስማቸው የከበረ ነው (ዘፍ.12÷12)፡፡ ኅብቸው የከበረ ነው፣ ልብሳቸው ፈዋሽ ነው፣ ዐፅማቸው የከበረ ነው፡፡ (2ኛ ነገ.13÷20 ፣ የሐዋ.ሥራ 19÷11-12)፡፡ የጸጋ ስግደት ይሰገድላቸዋል (1ኛ ነገ.18÷ት ፣ 2ኛ ነገ.1÷13)፡፡